ደቦ ማይክሮፋይናንስ ኢንስቲትዩሽን አ.ማ.
Debo Microfinance Institution S.C.

ቁጥር፡- DMFI/HO/1698/24
ቀን፡- 30/12/2016 ዓ.ም

ለሁሉም የደቦ ማይክሮ ፋይናንስ ኢንስቲትዩሽን አ.ማ ባለአክሲዮኖች
አዲስ አበባ

ጉዳዩ፡- ለ9ኛ መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ ስብሰባ ላይ እንዲገኙ ጥሪ ለለማድረግ ይሆናል።

በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ንግድ ሕግ አንቀጽ 366(1)፣ 367 (2) እና 370 እንዲሁም በአክሲዮን ማህበሩ መመስረቻ ጽሑፍ አንቀጽ 20 መሠረት የደቦ ማይክሮ ፋይናንስ ኢንስቲትዩሽን አክሲዮን ማህበር የባለአክሲዮኖች 9ኛ መደበኛ አመታዊ የጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባ ጥቅምት 02 ቀን 2017 ዓ.ም ከቀኑ 8:00 ሰዓት እስከ 11:30 ሰዓት በአዲስ አበባ ሳሮ ማሪያ ሆቴል የስብሰባ አዳራሽ ውስጥ ይካሄዳል።
በመሆኑም የተከበራችሁ የደቦ ማይክሮ ፋይናንስ ኢንስቲትዩሽን አ.ማ ባለአክሲዮኖች ወይም በሕጋዊ ወኪሎቻችሁ አማካኝነት በአካል በተጠቀሰዉ ቀን፣ ሰዓትና ቦታ በጉባዔው ላይ እንዲትገኙ የዳይሬክተሮች ቦርድ ጥሪውን በአክብሮት ያቀርባል።

1. የአክሲዮን ማህበሩ ዋና ዋና መረጃዎች
   1.1 የአክሲዮን ማህበሩ ዋና መ/ቤት አድራሻ፡ አዲስ አበባ ቦሌ ክ/ከተማ ቲኬ ሕንጻ
   1.2 የአክሲዮን ማህበሩ የምዝገባ ቁጥር፡ MT/AA/3/0041241/2010
   1.3 የአክሲዮን ማህበሩ ባለአክሲዮኖች ብዛት 134 ሲሆን የተፈረመ ካፒታል ብር 84,305,000
   1.4 የአክሲዮን ማህበሩ የተከፈለ ካፒታል ብር 76,890,633
   1.5 የአክሲዮን ማህበሩ ድሬ ገፅ WWW.debomicrofinance.com
2. የ9ተኛ መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ አጀንዳዎች
   2.1 አክሲዮን የገዙ አዳዲስ ባለሀብቶች መቀበልና አክሲዮን ያሳደጉ ነባር ባለአክሲዮኖችን ማስተዋወቅ፣
   2.2 የዳይሬክተሮች ቦርድ ሪፖርት መስማትና ተወያይቶ ማጽደቅ፣
   2.3 የአክሲዮን ማህበሩ የውጭ ኦዲተሮች ሪፖርት መስማትና ተወያይቶ ማጽደቅ፣
   2.4 የ2016 ዓ.ም ትርፍ አመዳደብና ክፍፍል ላይ ቦርዱ ባቀረበው የውሳኔ ሃሳብ ላይ መወያየትና መወሰን፣
   2.5 ለዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ለለሚከፈል ወራዊ አበል እና የትራንስፖርት አበል ለለማሻሻል ላይ መወያየትና መወሰን ናቸው።

ማሳሰቢያ

- በጉባኤው ላይ መገኘት የማይችሉ ባለአክሲዮኖች ተወካዮቻቸሁ ለልጣን ባለው የመንግስት አካል ተረጋግጦ የተሰጠ የውክልና ሰነድ ዋናውን እና ፎቶ ኮፒ በመያዝ ወይም በንግድ ሕግ አንቀጽ 377 መሠረት ጉባኤው ከመካሄዱ ከሦስት ቀን በፊት በዋና መ/ቤት ቢሮ ቦሌ ቲኬ ሕንጻ 1ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 111 በአካል በመቅረብ ለዚሁ ዓላማ በማህበሩ የተዘጋጀውን የውክልና ቅፅ ምልተው በመፈረም ተወካይ መሾምና ተወካይም የውክልና ማስረጃውን በመያዝ የጉባኤው ተካፋይ በመሆን ድምጽ ለመስጠት የሚችሉ መሆኑን በአክድሮት እንገልፃለን። ሆኖም አንድ ባለአክሲዮን በማህበሩ ጠቅላላ ጉበኤ በማንኛውም ችሎታ መወከል የሚችለው አንድ ሰው ብቻ ለለመሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል።
- ባለአክስዮኖቹ እና የባለአክሲዮን ተወካይ በጉባዔው ሲገኙ ኢትዮጵያዊነታቸውን የሚያረጋግጥ የታደለ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ዋናውን ከኮፒ ጋር ይዘው መገኘት ይኖርባቸዋል።

የደቦ ማይክሮ ፋይናንስ ኢንስቲትዩሽን አክሲዮን ማህበር የዳይሬክተሮች ቦርድ

ከሠላምታ ጋር

አማረ ፈለቀ ጋሻው
የዳይሬክተሮች ቦርድ ፕሬዝዳንት
Amare Feleke Gashaw